# ወጣትነት በምስራቅ ኢትዮጲያ፣ ሀረር – ክፍል ሁለት

November 21, 2017 - ትንታኔ

ኤድመን ተስፋዬ

ሀረር በምስራቁ የሀገራችን ክፍል ከሚገኙ ጥንታዊ ከተሞች መሀል ላቅ ያለ እድሜ ያላት ከተማ ነች፡፡ እ.ኤ.አ በ2007 በተካሄደው ሀገር አቀፍ የህዝብ ቆጠራ መሰረት የሀረር ህዝብ ብዛት 183,415 ነው፡፡ ህወሀት-ኢህአዴግ በምን መሰረት እንዳዋቀራቸው በከማይታወቁት ክልሎች በተለየ መልኩ የሀረር ከተማ ብዙሀኑ ህዝብ በከተማ የሚኖርባት ከተማ ነች፡፡ እ.ኤ.አ በ2007 በተካሄደው አጠቃላይ የህዝብ ቆጠራ መሰረት ከአጠቃላዩ የሀረር ህዘዝብ ውስጥ 56.41 ፐርሰንቱ ኦሮሞ ሲሆን፣22.77 አማራ፣ 8.65 ፐርሰንቱ ሀረሪ (በቀድሞ አጠራሩ አደሬ)፣ 4.34 ፐርሰንት ጉራጌ፣3.87 ፐርሰንት ሱማሌ፣1.53 ፐርሰንቱ ትግሬ እንዲሁም 1.26 ፐርሰንቱ የአርጎባ ብሄር ተወላጅ ነው፡፡ በሀረር ከተማ ህዝቦች የሚነገርን ቋንቋ በተመለከተ እ.ኤ.አ በ2007 የተካሄደው የህዝብ ቆጠራ የሚያሳየን 56.84 ፐርሰን የሀረር ህዝብ ኦሮምኛ ተናጋሪ ሲሆን፣ 27.53 ደግሞ አማርኛ ተናጋሪ ነው፡፡ ሀረሪ፣ ሶማሌ፣ትግራይ እና አርጎብኛ ተናጋሪ ህዝቦች ደግሞ እንደየቅደም ተከተላቸው7.33፣3.7 እና 2.9 ፐርሰንቱን ይይዛሉ፡፡ ከሀረር የአጠቃላይ ህዝብ ውስጥ 68.99 የእስልምና እምነት ተከታይ ሲሆን፣27.1 ፐርሰንቱ የኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ ነው፣ በተጨማሪም 3.4 ፐርሰንት የሚሆነው የሀረር ህዝብ ፕሮቴስታንቴ ፣ 0.3 ፐርሰንቱ የካቶሊክ፣ እንዲሁም የተቀረው 0.2 ፐርሰንቱ ደግሞ የባህላዊ እምነት ተከታዮች ናቸው፡፡

መስፈርቱ ምን እንደሆነ ለብዙሀኑ ግልፅ ባልሆነ ምክንያት ህወሀት – ኢህአዴግ ሀረርን እንዲያስተደዳር ለሀረሪ ህዝብ ሀላፊነቱን ከሰጠ ጀምሮ ሀረርን በማስተዳደር ላይ የሚገኘው ሀብሊ ነው፡፡ የሲዳማ ብሄርን የመሳሰሉ ብሄሮች ለብቻችን ክልል የሰጠን ሲሉ ከህወሀት ኢህአዴግ የሚሰጠውን መምላሽ ላስተዋለ የሀረር ህዝብ በሀብሊ የበላየረነት መተዳደሩ ላይ ጥያቄ ቢያነሳ አይገርምም፡ ፡ የሀረሪ ብሄራዊ ሊግ (ሀብሊ) ጥንታዊታን ሀረር ከተማን ማስተዳደር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ከተማዋ ከማደግ ይልቅ ባለችበት እንደቆመች፣ ነዋሪዎቿ ሀብሊ በፈጠረው የዘረኝነት ጦስ እየተለበለቡ ይገኛሉ፡፡

ጌታቸው ኢሳያስ እና ምንተስኖት እሸቱ በሀረር ከተማ የተወለዱ አብሮ አደግ ጓደኛሞች ናቸው፡፡ እኚህ ከደሀ ቤተሰብ የተወለዱት ሁለት ጓደኛሞች አስተዳደጋቸው እንደ አብዛኛው ኢትዮጲያዊ ነው፡፡ ጌታቸው ኢሳያስ እንደ አስራ ሁለተኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ሁሉ የዩኒቨርስቲ ትምህርቱን በጥሩ ውጤት አጠናቋል፡፡ ምንተስኖት በበኩሉ በሙያና ቴክኒክ ትምህርት ቤት በብረት ስራ የተመረቀ ወጣት ነው፡፡ ሁለቱ ጓደኛሞች ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በሁዋላ ወደ ስራ ፍለጋ ነበር ያመሩት፡፡ ምንተስኖት ከሰፈሩ ልጆች ጋር በመሆን ለኮንዶሚኒየም ቤቶች የሚሆን እና ለሌሎች ድርጅቶች በርና መስኮት እንዲሁም ሌሎች የብረት ውጤቶችን የሚሰራ ማህበር አቋቁመው ወደስራ ገቡ፡፡ ጌታቸው በበኩሉ ከዩኒቨርስቲ የተመረቀበትን ዲግሪ በመያዝ በሀረር ወደሚገኙ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ስራ ፍለጋ አመራ፡፡

ጌታቸው ኢሳያስ ስራ ፍለጋ ባመራባቸው በሀረር የሚገኙ የመንግስት መስሪያቤቶች ከዲግሪው ይልቅ ሲጠይቁት የነበረው የክልሉን ቋንቋ ስለመቻሉ ነበር፡፡ በሀረር ተወልዶ ላደገው ጌታቸው ኢሳያስ ይህ ክስተት አስደንጋጭ ነበር፡፡ በሀረር ከተማ ተወልዶ ያደገ ከሀረሪ ብሄር ውጪ ያለ ወጣት ሀብሊ በሚያስተዳድራት ሀገሩ ስራ የማግኘቱ ነገር የማይታሰብ ነው፡፡ ብዙሀኑ በሀረር ተወልደው ያደጉ ወጣቶች በተወሉዱበት ሀገር ሀረር እንደ ጠራጊ፣ተላላኪ፣መዝገብ ቤት ባሉ የስራ መስኮች እንጂ በተማሩበት የሙያ ዘርፍ በመንግስት ቤት የመስራታቸው ነገር የማይታሰብ ነው፡፡ በሀገራችን ከተሞች በላቀ መልኩ የሀረር ወጣት ሀብሊ በሚያደርስበት አድሎ የተነሳ ከተማዋን ጥሎ ወደ ጎረቤት ከተሞች፣ ድሬደዋ መሰደዱ የተለመደ ነው፡፡ ከከተማዋ የወጣቶች መፍለስ ጋር በተገናኘ ሊጠቀስ የሚገባው በሺህ የሚቆጠር በሀብሊ አመራር የገፋው የሀረር ወጣት የአንድ አመት የመምህራርንነት ስልጠና ወስዶ ወደ አፋር፣አማራ ክለል፣ወደ ድሬደዋ የገጠር ቀበሌዎች የመፍለሱ እና የመሰደዱ ነገር ነው፡፡

በሌሎች የሀገሪቱ ክልሎች እንደተጀመረው ሁሉ በሀረሪ ክልል ወጣቶችን በማህበር በማደራጀት ብድር በማበደርና በማህበራት በማደራጀት በጥቃቅንና አዘነስተኛ ስራ ላይ ተሰማርተው ነበር፡፡ ጉድ እና ጅራት ከሁአላ ነው እንዲል የሀገሬ ሰው የማህበራቱ ዘላቂነት ግን ያው እንደተለመደው ከብሄር ጋር የተገናኘ ሆነ፡፡ በሀረር በአብዛኛው የሀረሪ ብሄር በማይበዛባቸው ቀበሌዎች አልያም የሀረሪ ብሄር በአባልነት በሌለባቸው በማህበራቱ እንደተለመደው የሀብሊ የዘረኝነት አሰራር እምብዛም አላስኬዳቸውም፡፡ በሚያስገርም መልኩ በሀረሪ ክለል በአለም ባንክ እርዳታ ለኮብል እስቶን ማንጠፊያነት እንዲውል ተብሎ የተገኘውን ብዙ ሚሊየን ብር እነዚህ ማህበራት ብሩን ማግኘት ሲገባቸው የሀረሪ ብሄራራዊ ሊግ ቱባ ባለስልጣናት የማህበራቱን

ፍቃድ በመጠቀም መስራታቸው ነበር፡፡ ሌላው በሚገርም ሁነታ ከማህበራት ጋር በተገናኘ በሀረር ያከው አሰቃቂ ነገር የሀረሪ ልማት ማህበር ሳምቲ በማህበር አደራጅቶ በጀጎል ዙሪያ ያሰባሰባቸው ወጣቶች እና አዛውንቶች ላለፉት ሁለት አስርት አመታት ሲዘልቁ እንደ እድገት በህብረት፣ጋራ ለለረማት የተባሉ ከሀረሪ ብሄር ውጪ ያሉ የሌላ ብሄር ተወላጆች በብዛት የሚገኙባቸው ማህበራት ከአንድ አመት በላይ መዝለቅ አለመቻላቸው ነው፡፡

ምንተስኖት ከሰፈሩ ልጆች ጋር በመህበር ተደራጅቶ ይሰራው የነበረው የብረት ስራ ሀብሊ በሚያስተዳድራቸው የቤቶች ኤጀንሲ እና የጥቃቅን እና አነስተኛ ማደራጂያ ቢሮ ቅጥ ያጣ ዘረኝነት እና ቢሮክራሲ የተነሳ ከአንድ አመት በላይ ሊዘልቅ አልቻለም፡፡ የነ ምንተስኖት ማህበር አንድ አመት ሙሉ እየሰራ ያገኘውን ገቢ ከሀረሪ ጥቃቅን እና አነስተኛ ቢሮ በከፍተኛ ወለድ የተበደረውን ብር ከመክፈል እና በእዳ ከመነከር ባለፈ ለማህበሩ አባላት ያተረፈው ምንም ነገር የለም፡፡ በሚያሳዝን መልኩ በነ ምንተስኖት የማህበር ፍቃድ የሀብሊ ቱባ ባለስልጣናት ዘመዶች እና ወዳጆች እነ ምንተስኖትን ቀጥረው ለጋራ መኖሪያ ቤት የሚሆን እንደ የብረት በር፣መስኮት መወጣጫ አሰርተው ዳጎስ ያለ ብር መስራታቸው ነው፡፡ በዚህ አይነቱ የተሳከረ የሀብሊ ዘረኝነት የተነሳ የነምንተስኖት ማህበር ሲፈርስ የማህበሩ አባላት ግማሾቹ ወደ ድሬደዋ እና ወደ መሀል ሀገር ሲፈልሱ ምንተስኖት የባጃጅ መንጃ ፍቃድ በማውጣት ሀረር ከተማ ላይ ባጃጅ መንዳት ጀመረ፡፡

የሀብሊ የዘረኝነት በትር አላሳራ ያላቸው ብዙሀኑ የሀረር ወጣቶች ከማህበራቱ መፈራረስ በሁአላ ፊታቸውን ያዞሩት ወደ ባጃጅ ሹፌርነት ነበር፡፡ እዚህም እሳት አለ እንዲሉ የሀብሊ የዘረኝነት ብትር በባጃጁም ቢሆን አልቀረላቸውም፡፡ ከባጃጅ ትራንስፖርት ጋር በተገናኘ በሀረር ከተማ በሀብሊ ቱባ ባለስልጣናት መሪነት የሚከወነው ህገ ወጥ ተግባር ከትራፊክ ፓሊስ ቅጣት እና ከመንጃ ፍቃድ ጋር እንዲሁም የሀረሪ መንገድ ትራንስፖርት መስሪያቤት በመስሪያቤትነት የሚጠቀምበትን ባለ አራት ፎቅ ህንፃ ኪራይ ጋር የተገናኘ ነው፡፡ በሀረር ከተማ ባጃጅን ጨምሮ የሌሎች መኪናዎችን የማሽከርከሪያ ፍቃድ የሚሰጡት እንደ አዜብ፣ሳቢት የመሳሰሉ የሐረሪ ብሄር ተወላጆች በባለቤትነት የሚያስተዳድሯቸው ተቋማት ናቸው፡፡እነዚህ ተቋማት የባጃጅ መኪና ለመንዳት የሚረዳ መንጃ ፍቃድ አስተምሮ ለመስጠት እስከ ስድስት ሺህ ብር ይጠይቃሉ፡፡

የሀረሪ መንገድ ትራንስፓርት መስሪያቤት በመስሪያቤትነት የሚጠቀምበትን ባለ አራት ፎቅ ህንፃ ዳጎስ ባለ ወርሀዊ ክፍያ የተከራየው ከአንድ የሀረሪ ብሄር ተወላጅ ግለሰብ ነው፡፡ በሚያስገርም ሁኔታ የሀረሪ መንገድ ትራንስፓርት መስሪያቤት በመስሪያቤትነት የሚጠቀምበትን ይህን ባለ አራት ፎቅ ህንፃ ወርሃዊ የኪራይ ገንዘብ ለመክፈል ወሩ በደረሰ ቁጥር በሀረር ከተማ ካሉት ባጃጆች ስነስርአቱን ጠብቀው ከሚሰሩት ቅጣት ቢል የዳቦ ስም በትንሹ መቶ ብር መውሰድ ባህል ሆኗል ሀብሊ በሚያስተዳድራት ሀረር፡፡ ሌላው ከባጃጅ ጋር በተገናኘ በሀረር ያለው ጉድ የሀረሪ ብሄራዊ ሊግ ቱባ ባለስልታናት ባለቤትነት ከተያዙት ባጃጆች ጋር ይገናኛል ፡፡ እነዚህ በተለምዶ ይለፍ በማባል የሚጣወቁት ባጃጆች የፈለጉትን ሰው ከህግ አግባብ ውጪ ቢጭኑ፣ ያለቦታቸው ቢቆሙ በሀረሪ ትራፊክ ፓሊስ የማይቀጡ ናቸው፡፡

ሌላው ሀብሊ በበላይነት በሚመራት ሀረር ያለው ህገወጥነት፣ከቀበሌ ቤቶች፣ከኮንዶሚኒየም ባለቤትነት እና የመንግስት ቤቶች ጋር የተገናኘ ነው፡፡ በህግ እንደሰፈረው አንድ ግለሰብ ከቀበሌ የተከራየውን ቤት መልቀቅ ቢፈልግ ቁልፉን ለቀበሌው መመለስ እንጂ ለሌላ ሰው መሸጥም ሆነ በነፃመስጠት እንዲሁም ማከራየት አይችልም፡፡ በሀረር ከተማ ግን ነገሩ የተገላቢጦሽ ነው፡፡ አንድ ከሀረሪ ብሄር ውጪ ያለ በቀበሌ ቤት ውስጥ የሚኖር ግለሰብ የሚኖርበትን ቤት ህግን በመጣስ መሸጥ ቢፈልግ መሸጥ የሚችለው ለሀረሪ ብሄር ተወላጅ ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህን ሕገወጥ ድርጊት ህጋዊ በማስመሰል የቤቱን ስም ወደ ገዢ ማዞር የሚችሉት የሀረሪ ብሄር ተወላጆች ብቻ ስለሆኑ ነው፡፡ በዚህ አካሄድ ስንቱ የሀረሪ ብሄረሰብ ተወላጅ የቤት ባለቤት የመሆኑ ሁነት በሀረር ፍንትው ያለ ሀቅ ነው፡፡ ከኮንዶሚኒየም ጋር በተያያዘ የክልሉን ፕሬዝዳንት አቶ ሙራድን ጨምሮ ቱባዎቹ የሀብሊ ባለስልጣናት ከአራት እና አምስት በላይ የኮንዶሚኒየም ቤት ባለቤት የመሆናቸው ነገር ለሀረር ህዝብ እንግዳ አይደለም፡፡ የኮንዶሚንየም ባለቤትነትን በብሄር ደረጃ ሀረር ላይ ካየነው ከየትኛው ብሄር በተለየ በአብዛኛው የኮንዶሚኒየም ባለቤት ሀረር ላይ የሀረሪ ብሄር ተወላጅ ግለሰብ ነው፡፡ ሌላው ከቤት ጋር በተገናኘ በሀረር ያለው አይን ያወጣ ሌብነት የሀብሊ ቱባ ባለስልጣናት በስልጣን ላይ ሳሉ በመኖሪነት እንዲያገለግላቸው የተሰጣቸውን የመንግስት ቤት ስልጣን ከለቀቁ በሁአላ የቤቱን ባለቤትነት በስማቸው አዙረው ቤቱን የግላቸው ማድረጋቸው ነው፡፡ ለዚህ ማስረጃ ከተፈለገ የቀድሞው የሀረር የፓሊስ ኮሚሽን በስልጣን ላይ ሳለ የተሠጠውን ከደሴ ሆቴል ጎን ያለውን የመንግስት ቤት ስልጣን ከለለቀቀ በሁአላ መመለስ ሲገባው ቤቱን በስሙ አዙሮ እስከ አሁን ድረስ በቤቱ መኖሩን ማቅረብ ይቻላል፡፡

ከቀትር በሁአላ የሀብሊ ባለስልጣኖች በቢሮአቸው በማይገኙበት ሀረር ከተማ ለብዙሀኑ ህዝብ ግራ በሚያጋባ መልኩ እና የማእከላዊ መንግስቱን መንግስት እና ሀይማኖት የተለያዩ ናቸው የሚለውን የሀገሪቷን ህገ መንግስት መተፃረረ መልኩ የክልሉ መንግስት አልኮል እና ቢራ በመሸጥ ህዝቡን የሚያገለግሉ ሆቴሎችን በግብር ወዘተ ጋር ተገናኘ በሆኑ መንግስታዊ ምክንያቶች ማዋከቡ የተለመደ ነው፡፡ ሌላው ከሆቴሎች ጋር በተገናኘ በሀረር ያለው አሳዛኝ ነገር ለቱሪስቶችም ሆነ ለሀገር ውስጥ እንግዶች እና ለነዋሪዎቿ አገልግሎት የሚሰጥ ዘመናዊ ሆቴሎች በዘመነ ሀብሊ ያልተገነባላት መሆኑነ ነው፡፡

በሀረር ከተማ እንደ ጌታቸው እና ምንተስኖት አይነት ተመሳሳይ ታሪክ ያላቸው ወጣቶች በዛ ያሉ ናቸው፡፡ የጌታቸው እና የምንተስኖት ታሪክ በሀረር የሚገኙ ወጣቶችን የማህበራዊ እና የኢኮኖሚ ሁነት የሚገልፅ ነው፡፡ ተወልደው ባደጉበት ከተማ፣ አባቶቻቸው ሀገራቸውን ከውጪም ሆነ ከውስጥ ወራሪ ለመከላከል ሲሉ ደማቸውን እና አጠንታቸውን በከሰከሱበት ሀገር፣ ቋንቋ፣ ብሄር ስራ ለማግኘት እንደ ቅድመ ሁኔታ ተቀምጦ ሳለ በህገመንግስቱ የተቀመጠውን ማንኛውም ኢትዮጲያዊ ሰርቶ ሀብት የማፍራት መብት አለው የሚለውን ህግ በሚንድ መልኩ የሀረር ወጣቶች በከተማቸው የክልሉን ቋንቋ አትችሉም በሚል ብቻ የወጣትነታቸውን እድሜ በአልባሌ ነገር እንዲያሳልፉት ሀረርን የሚመራው ሀብሊ አስገድዷቸዋል፡፡

አንድም በህወሀት ኢህአዴግ የተሳከረ የኢኮኖሚ ፓሊሲ በፈጠረው የኑሮ ውድነት ሁለትም በሀብሊ የዘረኝነት አስተዳደር ወጣቶቿን በሁለት ቢላዋ የምታርደው ሀረር እስከመቼ ነው ለወጣቶቿም ሆነ ለብዙሀኑ ህብረተሰቧ ሲኦል ሆና የምትቀጥለው የሚለው አሁን ላይ በሀረር ከተማ እና አካባቢዋ ባሉ ብዙሀኑ ህዝብ የሚጠየቅ ጥያቄ ሆኗል፡፡